## የEBT ካርድ መረጃ (የገጽ ርእስ)

## የEBT ካርድዎን  መቀበል

ለ COVID-19 (coronavirus) ምላሽ ለመስጠት፣ DHS ከኤፕሪል 20 ጀምሮ አዲስ እና ምትክ ካርዶችን በፖስታ የመላክ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። ደምበኞች ካርዳቸውን በፖስታ እንዲደርሳቸው ከአምስት (5) እስከ ሰባት (7) የስራ ቀናት ይወስዳል። የEBT ካርዶች በአሁን ጊዜ በፖስታ እየተላኩ በመሆኑ፣ አዲስ ደምበኞች ወይም ምትክ ካርድ የሚጠይቁ ደምበኞች ካርድ ለማግኘት የ EBT ካርድ ስርጭት ማእከልን መጎብኘት አያስፈልጋቸውም። ቋሚ የመላኪያ አድራሻ የሌላቸው ደምበኞች የ EBT ካርዳቸውን በ645 H Street NE ወይም 1649 Good Hope Rd SE በሚገኘው የEBT የስርጭት ማእከላት ጋር በመሄድ መውሰድ ይችላሉ።

<u>የEBT የስርጭት ማእከል ሰዓታት</u> (H Street NE አድራሻ)

- እሮብ ከ7:30 ጥዋት – 12 እኩለቀን*
- ሰኞ ከ7:30 ጥዋት – 4:45 ከሰዓት*
- አርብ ከ7:30 ጥዋት – 4:45 ከሰዓት*

<u>EBT የስርጭት ማእከል ሰዓታት</u> (1649 Good Hope Rd SE አድራሻ)

- ማክሰኞ ከ7:30 ጥዋት – 4:45 ከሰዓት*
- ሀሙስ ከ 7:30 ጥዋት – 4:45 ከሰዓት*

**ሰዓታት እና ቀናት ሊቀየሩ ይችላሉ።*

የEBT ካርዶች የሚላኩት ከDHS አይደለም። የEBT ካርዶች የሚላኩት የግዛቱ የ EBT ካርድ ኩባንያ ከሆነው፣ ከFidelity Information Services (ፊደልቲ የመረጃ አገልግሎቶች) (FIS) በባዶ ገጽ ላይ ነው።

## የEBT ካርድዎን እንዲሰራ ማድረግ

- ካርድዎን መጠቀም እንዲችሉ እርስዎ ወይም ስልጣን የተሰጠው ተወካይ እንዲሰራ ማድረግ አለባቹ።
- ስልጣን ያለው ተወካይ ማለት ጥቅማጥቅሞችዎን እንዲቀበልልዎ የመረጡት ሰው ማለት ነው። ስልጣን ያለው ተወካይዎን መለየት ያለብዎ የጽሁፍ ሰነድ ለአከባቢዎ የአገልግሎት ማእከል በማቅረብ ነው። የአገልግሎት ማእከላት ዝርዝር በዚህ ይገኛል፣ dhs.dc.gov/service/find-service-center-near-you።
- ካርድዎ እንዲሰራ ለማድረግ፣ የግል የመለያ ቁጥር (Personal Identification Number, PIN) ያስፈልግዎታል።
- ፒን (PIN) ለመፍጠር FIS ጋር በ(888) 304-9167 ይደውሉ። ፒን (PIN) ለመፍጠር የትውልድ ቀንዎን እና የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎ (SSN) የመጨረሻ አራት ቁጥሮች ያስፈልግዎታል። እርስዎ SSN ከሌሎት ወይም በሚያመለክቱበት ወቅት ካልሰጡ፣ PIN ለመፍጠር የትውልድ ቀንዎን እና ዚፕ ኮድ መጠቀም ያስፈልግዎታል።
- ፒንዎን (PIN) በአስተማማኝ ሁኔታ ይያዙ እናም ለማንም አያጋሩ። ፒንዎን (PIN) ማስታወስ ካልቻሉ ወይም አንድ ሰው ፒንዎን (PIN) ካገኙት፣ አዲስ ፒን (PIN) ለመምረጥ FIS ጋር በ(888) 304-9167 ይደውሉ።
- የካርድዎ ጀርባ ላይ ይፈርሙ እና ፒንዎን (PIN ) በካርድዎ ላይ አይጻፉ።

## የካርድ ቁጥር

የካርድ ቁጥርዎ በካርድዎ ፊት ለፊት ያለው ባለ 16 አሀዝ ቁጥር ነው።

## የ EBT ካርድዎን በአስተማማኝ ሁኔታ ይያዙት እና ማንኛውም ችግሮች ካሉ ሪፖርት ያድርጉ

- ፒንዎን(PIN) ለማንም ሰው አይስጡ።
- እሱ ወይም እሷ DHS ጋር የተመዘገቡ ስልጣን ያላቸው ተወካይዎ ካልሆኑ በስተቀር፣ ካርድዎን ለማንም ሰው አይስጡ።
- ካርድዎን አይጣሉ። ጥቅማጥቅሞች በየወሩ እሱ ላይ ይሞላሉ።
- ካርድዎ ከጠፋ፣ ከተሰረቀ፣ ወይም ከተበላሸ እና ምትክ የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ FIS ጋር በ(888) 304-9167 ይደውሉ።
- ጥቅማ ጥቅሞችዎን ለማግኘት መዘግየት እንዳይኖር የEBT ካርድዎን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው።

## በEBT ካርድዎ ላይ ያሉት ጥቅማጥቅሞች

- በእያንዳንዱ ወር፣ ጥቅማጥቅሞችዎ በካርድዎ ላይ ይሞላሉ።
- ጥቅማጥቅሞችዎን የጥሬ ገንዘብ ለማግኘት ወይም እቃዎችን ለመግዛት ሲጠቀሙ፣ ያለዎት ቀሪ ሂሳብ ይቀንሳል።

የተጨማሪ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም( SNAP) ጥቅማጥቅሞች በአያት ስምዎ የመጀመሪያ ፊደል መሰረት፣ በየወሩ በተመሳሳይ ቀን፣ ቀኑ በሳምንቱ የእረፍት ቀናት ወይም በበዓል ቀን ቢውልም እንኳን በካርድዎ ላይ ይገኛል። ከታች ያለውን የጊዜ ቀጠሮ ሰንጠረዥ ይመልከቱ። የ SNAP ጥቅማጥቅሞች ምግብ ለመግዛት ብቻ ናቸው። የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞች በወሩ የመጀመሪያው ቀን ይገኛሉ። ሁሉም ጥቅማጥቅሞች ከጥዋቱ 5 ሰዓት በኋላ ይገኛሉ።

| የአያት ስምዎ የሚጀምርበት ፊደል ፣ | የSNAP ጥቅማጥቅሞችዎን ያገኛሉ በ፣ |
|---|---|
| A ወይም B | የወሩ 1ኛ ቀን |
| C | የወሩ 2ኛ ቀን |
| D፣ E፣ ወይም F | የወሩ 3ኛ ቀን |
| G ወይም H | የወሩ 4ኛ ቀን |
| I፣ J ወይም K | የወሩ 5ኛ ቀን |
| L ወይም M | የወሩ 6ኛ ቀን |
| N፣O፣ P ወይም Q | የወሩ 7ኛ ቀን |
| R ወይም S | የወሩ 8ኛ ቀን |
| T፣ U፣ ወይም V | የወሩ 9ኛ ቀን |
| W፣X፣ Y ወይም Z | የወሩ 10ኛ ቀን |

## ገበያ ከማድረግዎ በፊት የ EBT ካርድዎ ላይ ያሎትን ቀሪ ሂሳብ ያረጋግጡ

- በካርድዎ ላይ ያለው የጥቅማጥቅሞች መጠን በመጨረሻው የመደብር ደረሰኝዎ ላይ ይጻፋል።
- በተጨማሪ ያሎትን ቀሪ ሂሳብ ኢንተርኔት ላይ በwww.ebtedge.com ማረጋገጥ ወይም የ EBT Edge የሞባይል መተግበሪያውን ከአፕል የመተግበሪያ መደብር ወይም ከ ጉግል ፕሌይ መደብር በማውረድ የነበረውን የግብይት ታሪክ፣ ቀሪ ሂሳብዎን፣ ወይም የEBT ካርዶችን የሚቀበሉ መደብሮችን ማየት ይችላሉ። በተጨማሪ ቀሪ ሂሳብዎን በ FIS (888) 304-9167 በመደወል ማረጋገጥ ይችላሉ።

## የተፈቀደ የEBT ጥቅማጥቅሞች አጠቃቀም

የEBT ካርድዎን በምግብ መደብሮች እና ማንኛውም ለመቀበል የተፈቀደላቸው ችርቻሮ ነጋዴዎች ጋር መጠቀም ይችላሉ። ካርድዎን በመሸጫው ተርሚናል ላይ ያንሸራቱት ወይም ካርድዎን ለሻጩ ወይም ለገንዘብ ያዡ ይስጧቸው። SNAP እና የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞችዎን የተፈቀደላቸው ቸርቻሪዎች ጋር ሲጠቀሙ ምንም ክፍያ የለውም። ለሻጩ ወይም ለገንዘብ ያዡ ከየትኛው ሂሳብ ላይ ከSNAP ወይም በጥሬ ገንዘብ መሰላት እንዳለበት ይንገሯቸው። ፒንዎን (PIN ) ማስገባት አለብዎ። ሻጩ ወይም ገንዘብ ያዡ በደረሰኙ ላይ ያለው መረጃ ትክክል መሆኑን የሚያረጋግጥ የደረሰኝ ማረጋገጫ ይሰጥዎታል።

### የSNAP ጥቅማጥቅሞች

የSNAP ጥቅማጥቅሞች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉት ምግብ ከምግብ መደብሮች፣ ከገበሬዎች ገበያዎች፣ ወይም ሌሎች የተፈቀደላቸው የችርቻሮ ነጋዴዎች ወይም ኦንላይን Amazon.com ጋር ለመግዛት ነው። በአቅራቢያዎ ያለውን መደብር ለማግኘት፣ ይሂዱ here። የ SNAP ጥቅማጥቅሞችዎን አማዞን ላይ ለመጠቀም፣ ይሂዱ እዚህ፣ እና በማሳያ ገጹ ላይ ያሉትን መመሪያዎች ይተግብሩ።

የሚከተሉት የምግብ አይነቶች በ SNAP ጥቅማጥቅሞችዎ ሊገዟቸው የሚችሏቸው ናቸው፣

- ፍራፍሬዎች እና አትክልቶች፣
- ስጋ፣ ዶሮ፣ እና አሳ፣
- የወተት ተዋጽኦዎች
- ዳቦዎች እና ሲሪያሎች
- ሌሎች ምግቦች እንደ የቡና ቁርስ እና የመክሰስ ምግቦች እና አልኮል የሌላቸው መጠጦች፣ እና
- ቤተሰቡ የሚመገበውን ምግብ የሚያመርቱ፣ ዘሮች እና አትክልቶች።

የመሸጫው ተርሚናል የማይሰራ ከሆነ እና እንደዛም ሆኖ እርስዎ መግዛት ከፈለጉስ?

- ሻጩ የምግብ ጥቅማጥቅም ደረሰኝ የተባለ የወረቀት ቅጽ ይሞላሉ። **ለገንዘብ ያዡ ፒንዎን (PIN ) አይስጡ።**
- ገንዘብ ያዡ የካርድ ቁጥርዎን እና ያወጡትን የገንዘብ መጠን ይጽፋሉ እና እቃዎቹን ለመግዛት በካርድዎ ላይ በቂ የSNAP ጥቅማጥቅሞች ያሎት መሆኑን ለማረጋገጥ ይደውላሉ። እርስዎ በቂ የSNAP ጥቅማጥቅሞች ካሎት፣ እቃዎቹን መግዛት ይችላሉ፣ ደረሰኙን መፈረም ይኖርብዎታል፣ እና የሱን ቅጂ ያገኛሉ።
- መደብሮች ደረሰኞችን ለጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞች መጠቀም አይችሉም።

### የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞች

የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞች ካሎት፣ እነሱን እንደ ጥሬ ገንዘብ መጠቀም ይችላሉ። በተጨማሪ የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞችዎን ለገዙት እቃዎች የጥሬ ገንዘብ መልሰው ለማግኘት መጠቀም ይችላሉ። የጥሬ ገንዘብ ማውጣት የሚችሉት ከተሳታፊ ATM (ኤቲኤሞች) ብቻ ነው። ከጥሬ ገንዘብ ሂሳብዎ የጥሬ ገንዘብ ለማውጣት ወደ ባንክ መሄድ አይችሉም። ከካርድዎ የጥሬ ገንዘብ ብቻ ማውጣት ይችላሉ – ገንዘብ ማስቀመጥ አይችሉም። የመጀመሪያዎቹ ሁለት የATM ወጪዎች በየወሩ ነጻ ናቸው፣ እና ማንኛውም ተጨማሪ ወጪዎች እያንዳንዱ $0.85 ያስከፍልዎታል።

ጥሬ ገንዘብ ለማውጣት፣ ATM ጋር የሚከተሉትን እርምጃዎች ይከተሉ፣

- የEBT ካርድዎን ያስገቡ ወይም ያንሸራቱ።
- ፒንዎን (PIN) ያስገቡ እና ከዚያ አዎ ወይም አስገባ የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።
- የጥሬ ገንዘብ ማውጣት የሚለውን ይምረጡ እና ከዚያ ማረጋገጥ የሚለውን ይምረጡ።
- ማውጣት የሚፈልጉትን መጠን በዶላር መጠን ያለ ነጠላ ሰረዝ ያስገቡ።
- ካርድዎን፣ ደረሰኝዎን፣ እና ጥሬ ገንዘብዎን ይውሰዱ።

## የ EBT ካርድ እና ጥቅማጥቅሞችን በትክክል አለመጠቀም/አለአግባብ መጠቀም

- ጥቅማጥቅሞችዎን በሚመለከት በማጭበርበር ተግባር መሳተፍ ወይም ካርድዎ አለአግባብ መጠቀም ወንጀል ነው።
- የግዛት እና / ወይም የፌዴራል ባለስልጣናት በትክክል አለመጠቀምን ወይም አለአግባብ መጠቀምንይመረምራሉ ፣ ይህም ከጥቅማጥቅም ፕሮግራሞች መሰረዝን፣ የተወሰዱ ጥቅማጥቅሞች እንዲመለሱ ማድረግን፣ እና የወንጀል ክስ እንዲቀርብ ጥያቄ እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል።
- ጥቅማጥቅሞች የማይተላለፉ ናቸው። የምግብ ወይም የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞችዎን ለሌሎች ሰዎች መስጠት ወይም መሸጥ ህገወጥ ነው።

## የመላኪያ አድራሻዎን ወቅታዊ ያድርጉ

- አድራሻዎችዎን በቀየሩ ቁጥር፣ ጥቅማጥቅም በማግኘት ላይ ምንም መቋረጥ አለመኖሩን እና ሁሉም ማስታወቂያዎችን ማግኘትዎን ለማረጋገጥ ለDHS አዲሱ አድራሻዎን ያሳውቁ።
- የጥሪ ማእከል ጋር በ(202) 727-5355 በመደወል ወይም የ DHS የአገልግሎት ማእከል በ(dhs.dc.gov/service/find-service-center-near-you) በመጎብኘት የመላኪያ አድራሻዎን DHS ጋር ወቅታዊ ያድርጉ።

## የ EBT ካርዶችን እንዴት መቀበል፣ እንዲሰራ ማድረግ እና መጠቀም እንድሚችል መረጃ ያለው ቪድዮ

- ይህ የEBT ካርድዎን እንዴት ማግኘት፣እንዲሰራ ማድረግ፣ እና መጠቀም እንደሚችሉ የሚያሳይ የ እንግሊዘኛ እና የስፓኒሽ ቪዲዮ ነው። እባክዎ ለመመልከት ጊዜ ይውሰዱ።